# Amharic, 2015 EC, Grade 6 model exam, Yeka

Grade 6 · Amharic · 2015 E.C.

**Time allowed:** 120 minutes **Questions:** 49 **Total marks:** 49

Name ______________ Grade ________ ID No. ________ Date ________

**1.** ምንባብ አሊ አምስት ዓመት እንኳን ሳይሞላው ነበር የሞቱት። በአብዛኞቹ የገጠር ልጆች ላይ እንደሚሰራው ሁሉ አሊም እረኝነት እጣው ፈንታው ሆነ። አንድ ቀን አሊ አጭር ግራር ሥር በሐሩር ጉልበት ተሸንፎ በራበው ሆዱ ተኝቶ ሳለ ከጆሮው ራቅ ወደጆሮው ቀረብ ራቅ ቀረብ የሚል ደስ የሚል ድምፅ ሰማ። ከሚያንጎላጅበት ቀና ሲል ድምፁ የሚመጣበትን አንድ ሸማግሌ ገበሬ የሚኖሩባትን እንዲት ደሳሳ ጐጆ ፈትለፊቱ አየ። አንዴ ቆም ብሎ እየሰማ አንዴ ወደ እሳቸው እየተጠጋ ቆሞ እያዳመጠ ወደ ጎጆዋ እየተጠጋ እየቆመ እየተራመደ ፊታቸው ተገተረ። በቀኝ ክንዳቸው ስር የሸጎጡዋትን ጥቅርሻ የለበሰች ክራር እየገፋ ቀና ብለው በትናንሽ አየኖቻቸው አዩት። አሊም በፀሀይ ግለት ያብረቀረቀ የጠቆረ ፊቱን እያሸ ሸማግሌው እግር ስር ቁጭ አለ። የጰጰስ ቆብ መስሎ ከተራሮች መኻል የጎላ ተራራ ሆኖ ጠፍጣፋ ምድር ላይ የተተከለው ዳዳምስ እየመሸ ሲሄድ ግዝፈቱና ግርማው መታየቱ ቀርቶ እየሟሟ ሲጠፋ የሸማግሌው ድምፅና የክራር ግርፍ ብቻ አካባቢውን ዋጠው ። በአንድ ክንዱ ተደግፎ አቦ "ፋርጤን ፊታቸውንና ሁኔታቸውን በአይኑ እይቃኘ ሲያዳምጥ "መሽብህሒድ! በጎችህም እንዳይጣፋብህ" አሉትና በአንድ እጃቸው ራሱን ዳበሱት። አሊ በክራር ፍቅር ያኔ ነበር የተለከፈው። ምንጭ ኤክስትሪም አማርኛ 5-8 ክፍል የተወሰደ • አሊ እናቱን በሞት ያጣው መቼ ነው? (1)

**A.** በአንድ ዓመቱ
**B.** በሁለት ዓመቱ
**C.** በሶስት ዓመቱ
**D.** አምስት ዓመት ሳይሞላው

**2.** አሊ ከሚያንጐላጅበት ቀና እያለ ጽምፅ የሚመጣበትን ቦታ አጣራ። የተሰመረበት ቃል አሊ በምን ሁኔታ ላይ እንደነበረ ይገልጻል? (1)

**A.** በለቅሶ ላይ
**B.** በሳቅ ላይ
**C.** በትዝታ ላይ
**D.** በእንቅልፍ ላይ

**3.** በምንባቡ እንደኛው አንቀጽ ውስጥ " ...በሐሩር ጉልበት ተሸንፎ " የሚለው ሐረግ ትርጉም ከሚከተሉት አማራጫች መካከል የትኛው ነው (1)

**A.** የስራጫና እስጎንብሶች
**B.** የፀሐይ ግለት አድክሞት
**C.** ጐልበተኛ ደብድቦ ጥሎት
**D.** ሰውዬው ተቆጥቶት

**4.** በሶስተኛው አንቀጽ ውስጥ ጥቅም ላይ ውለው የሚታዩት የስርዓተ ነጥብ አይነቶች ስንት ናቸው? (1)

**A.** ሁለት
**B.** ሶስት
**C.** አራት
**D.** አምስት

**5.** በአብዛኛው የገጠር ልጆች የሚሰሩት ሥራ ምንድን ነው (1)

**A.** የዋሸንት ጨዋታ
**B.** እረኝነት
**C.** ንግድ
**D.** ሹፌር

**6.** የሸማግሌው መኖሪያ ምን አይነት ነበር? (1)

**A.** ደሳሳ ጐጆ
**B.** የጎላ ተራራ
**C.** ከተራራው መሀል
**D.** ጠፍጣፋ ምድር ላይ

**7.** ሸማግሌው ክንዳቸው ስር የሸጉጡዋትን ጥቀርሻ የለበሰችው ምንድን ነበረች? (1)

**A.** ሹራብ
**B.** ክራር
**C.** ዋሽንት
**D.** ልብስ

**8.** " እየቃኘ" ሲል ምን ማለቱ ነው? (1)

**A.** እያመራ
**B.** እየተቀመጠ
**C.** እየተመለከተ
**D.** እየደነሰ

9. መመሪያ ሁለት ከተራ ቁጥር %1-) ለቀረቡት ሰዋሰዋዊ የምርጫ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያውን ፊደል ምረጥ /ጭ %1.ከሚከተሉት አማራጫች ውስጥ በፋቿ ልዩ የሆነው የቱ ነው (1)

A. ደከመ
B. ተመፀወተ
C. ለመነ
D. ቀላወጣ

10. ከሚከተሉት አማራጩች ውስጥ የተፀውኦ ስም የሆነው ምረጡ (1)

A. ሰለሞን
B. ወንበር
C. ወረቀት
D. ወንድ

11. ቀጥሎ ከቀረቡት መካከል የወል ስም የሆነውን መረጥ/ጭ (1)

A. ዳንኤል
B. ራስዳሽን
C. ኬንያ
D. ቤት

12. እመቤት ጐበዝ ተማሪ ናት። የአ/ነገሩ ባለቤት ----------- ነው (1)

A. ተማሪ
B. ጐበዝ
C. ናት
D. እመቤት

13. አንድ አይነት የሆኑ ነገሮች በጋራ የሚጠሩበት ስም /መጠሪያ ----------- ነው (1)

A. የተፀኦ ስም
B. የወል ስም
C. የጥቅልስም
D. የረቂቅ መጠሪ ስም

14. ትርጉም የሌለው ብቻውን መቆም የማይችል ምዕላድ ------ ይባላል (1)

A. ነፃ ምዕላድ
B. ጥገኛ ምዕላድ
C. ግስ
D. ባለቤት

15. " እየሄደች" የሚለው ምዕላድ ተተንትኖ ሲጻፍ ---------- ይሆናል (1)

A. እየ-ሔደች
B. እ-ሔደ-ች
C. እየ-ሔደ-ች
D. እ-የ-ሄ-ደ-ች

16. የአንቀጽ መሰረታዊ አካላት የምንላቸው የትኞቹ ናቸው (1)

A. ነፃ ምዕላድና ጥገኛ ምዕላድ
B. ባለቤትና ተሳቢ
C. ኃይለቃልና መዘርዝር
D. የወልና የተደውኦ ስም

17. አ/ነገሮች እርስ በርሳቸው ተገጣጥመው አንድ ነጠላ ሀሳብ ብቻ ለመግለፅ የሚያገለግል አነስተኛ የድርሰት ክፍል ------ ይባላል (1)

A. አንቀጽ
B. ድርሰት
C. አ/ነገር
D. ግጥም

18. ከሚከተሉት አማራጩች ውስጥ ነፃ ምዕላድ የሆነውን ቃል ምረጡ (1)

A. እርሳስ
B. አስደነገጠ
C. ወንበሩ
D. ቤቶች

19. በፅሁፍ ያለን መልዕክት/ሀሳብ በአግባቡ እንዲረዱት ያደርጋል (1)

A. ስርዓተ ነጥብ
B. የቃል ክፍሎች
C. አንቀጽ
D. ቢጋር

20. የአንቀጽን ቅርፅ የሚወሰንልን ምንድን ነው (1)

A. ግጥም
B. ኃይለቃል
C. መዘርዝር
D. ቢጋር

**21.** " እሱ"እሷ &እነሱ" የሚሉት ተውላጠ ስሞች ስንተኛ መደብ ናቸው? (1)

**A.** አንደኛ መደብ
**B.** ሁለተኛ መደብ
**C.** ሶስተኛ መደብ
**D.** መደብን አይገልጹም

**22.** ከሚከተሉት አማራጫች ውስጥ በብዙ ቁጥር የተገለፀው የቱ ነው (1)

**A.** መርከብ
**B.** በሬው
**C.** ወንበሮች
**D.** ልብስ

**23.** " ፃፈች" የሚለው ቃል በምን ጾታ ተገለጿል (1)

**A.** በተባዕታይ
**B.** በተባዕታይና በአነስታይ
**C.** በአነሰታይ
**D.** መልሱ የለም

**24.** '1.መሀመድ ሻይ ጠጣ። በሚለው አ/ነገር መሀመድ የሚለውን ስም የሚተካው የተውላጠ ስም የቱ ነው (1)

**A.** እሳቸው
**B.** እኔ
**C.** እናንተ
**D.** እሱ

**25.** '3ሰምሶም የክፍላችን አለቃ ነው። የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺው ---------- ነው (1)

**A.** ሀላፊ
**B.** ሀይለኛ
**C.** አሳዛኝ
**D.** ትሁት

**26.** '4.ይዘት /አንድ ነጥብ ለምን ያገለግላል (1)

**A.** አሳጥሮ ለመጻፍ
**B.** አጋኖ ለማቅረብ
**C.** ጥያቄ ለመጠየቅ
**D.** ተቃራኒ ሀሳብን ለመግለፅ

**27.** '5.ምዕላድ በስንት ይከፈላል (1)

**A.** በሁለት
**B.** በሶስት
**C.** በአራት
**D.** በአምስት

**28.** '6." እንግዳ " ለሚለው ቃል ተቃራኒውን ምረጡ (1)

**A.** ዘመድ
**B.** ወዳጅ
**C.** ቤተኛ
**D.** ዘመናዊ

**29.** '7.በሜዳው ላይ ነጭ ፍየል ይታያል። በአ/ነገሩ ውስጥ ያለው የስም ገላጭ --------- ነው (1)

**A.** ነጭ
**B.** በሜዳው
**C.** ላይ
**D.** ፍየል

**30.** '8." ከሰጠው " ይህ ቃል ቅጥያው በየት ቦታ ተቀጥሏል (1)

**A.** መነሻ ቅጥያ ብቻ ይዟል
**B.** መድረሻ ቅጥያ ይዟል
**C.** መነሻና መድረሻ ቅጥያ
**D.** ምንም ቅጥያ አልያዝም

**31.** (1.የግጥም አንድ መስመር ምን ይባላል (1)

**A.** ሐረግ
**B.** ስንኝ
**C.** ቤት
**D.** አንጓ

**32.** (2.ከሚከተሉት አማራÄች ውስጥ ከግጥም ቃላት ውስጥ ይመደባል (1)

**A.** አንቀጽ
**B.** ቤት መምቻ
**C.** አ/ነገር
**D.** ቅጥያ

**33.** (3.በአንድ ጉዳይ ላይ ብቻ ትኩረት የሚደርጉ የስንኞች ስብስብ -------- ይባላል (1)

A. ቤት
B. ቤት መምቻ
C. አንጓ/አርኬ
D. ስንኝ

**34.** (4ቃላዊ ግጥም ማለት የሰነቃል ዘርፍ ሲሆን በ ------- ሲተላለፍ የመጣ ነው (1)

A. በፅሁፍ
B. በመፅሐፍ
C. በደብዳቤ
D. በቃል

**35.** (5ቃላዊ ግጥም መቼ ይዜማል /ይገጠማል (1)

A. በሀዘን ጊዜ
B. በበዓላት ጊዜ
C. በስራ ጊዜ
D. ሁሉም መልስ ናቸው

**36.** (6.የቃላዊ ግጥም ደራሲ ማን ነው (1)

A. ማህበረሰቡ
B. ዘሪሁን አስፋው
C. ሀዲስ አለማየሁ
D. በአሉ ግርማ

**37.** (7.ይችን ማጭዴን ሆዷን አሟታል& እየቆረጠ ያጋድማታል ። ይህ ቃላት ግጥም በ --- ጊዜ ይዜማል (1)

A. በአጨዳ ጊዜ
B. በውቂያ ጊዜ
C. በቀረርቶ ጊዜ
D. በፉክራ ጊዜ

**38.** (8.እንጀራውን ጋግረሽ ከማን ጋር በላሽው& ጠላውንስ ጠምቀሽ ከማን ጋር ጠጣሽው& ደረት የሚመታ ጐረቤት ያጣሽው። ይህ ቃላት ግጥም ለምን አይነት ሴት የተገጠመ ነው (1)

A. ደግ በመሆኗ ለቅሶዋ ለደመቀላት ሴት
B. ዘመድ አልባ ሆና አልቃሽ ላጣች ሴት
C. ንፉግ በመሆኗ ለቅሶዋ እንደነገሩ ለሆነላት ሴት
D. ግጥሙ የሴትዮዋን ምንነት አይገልፅም

**39.** (9በተራ ቁጥር አርባ ስምንት ላይ የቀረበው ቃላዊ ግጥም ስንት ስንኞችን ይዟል (1)

A. ሶስት
B. አራት
C. አምስት
D. ስድስት

**40.** ሞፈሩ የብረት ቀንበሩም የብረት ምድርን ያረሰበት ----። ግጥሙን ሊያሟላ የሚችል መድረሻ ሀረግ ----- ነው (1)

A. እህል ያስቀመጠበት
B. ሰው ያፈረሰበት
C. እህል ያፈሰበት
D. ያዘነበት ሰዓት

**41.** መመሪያ ሶስት ከተራ ቁጠር )6 እስከ )5 ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ የያውን ቃል ምረጥ/ጭ )1.አፀፋ (1)

A. ውሸት
B. መንገድ
C. ምላሽ
D. ንዴት

**42.** ማጠራቀም (1)

A. መበታተን
B. ማከማቸት
C. ማስፋፋት
D. መስረቅ

**43.** አመል )3አመል (1)

A. ፀባይ
B. ባህሪ
C. ክፋ
D. ሀናለ መልስ ናቸው

**44.** ተስፋ (1)

A. ችሎታ
B. አጋጣሚ
C. ምኞት
D. ስልጠና

**45.** መመሪያ አራት ከተራ ቁጥር 56- 60 ለተዘረዘሩት ቃላት ተቃራኒያቸውን በመምረጥ መልስ/ሽ )6ማግኘት (1)

A. ማጐልበት
B. መኖር
C. ማፍራት
D. ማጣት

**46.** ባህላዊ (1)

A. የሚያምር
B. ዘመናዊ
C. ታሪክ
D. ግዙፍ

**47.** መብለጥ (1)

A. ማደግ
B. ማነስ
C. መውጣት
D. መታየት

**48.** በጋራ (1)

A. በአንድነት
B. በህብረት
C. በግል
D. ብዙ

**49.** ምስጢር (1)

A. ድብቅ
B. ውሸት
C. እውነት
D. ገሃድ

— END OF EXAMINATION —